የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETA

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

አሥራ ሰባተኛ ዓመት ቁጥር ፷፩
አዲስ አበባ ግንቦት ፲፫ ቀን ፪ሺ፫ ዓ.ም.

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝቦች ተወካዮች ምክር ቤት ጠቅላነት የወጣ

17th Year No. 61
ADDIS ABABA 23rd May 2011

ማውጫ

ደንብ ቁጥር ፪፻፴፩/፪ሺ፫
የሀዋሳ ዩኒቨርሲቲ እንደገና ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ..... ገፅ ፭ሺ፰፻፷፰

CONTENTS

Regulation No. 231/2011
Hawassa University Re-establishment Council of Ministers Regulation ..... Page 5868

## የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፪፻፴፩/፪ሺ፫

## ሀዋሳ ዩኒቨርሲቲን እንደገና ለማቋቋም የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈፃሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር ፮፻፺፩/፪ሺ፫ አንቀጽ ፭ እና በከፍተኛ ትምህርት አዋጅ ቁጥር ፮፻፶/፪ሺ፩ አንቀጽ ፭(፩) መሠረት ይህን ደንብ አውጥቷል ::

፩. አጭር ርዕስ

ይህ ደንብ "የሀዋሳ ዩኒቨርሲቲ እንደገና ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፪፻፴፩/፪ሺ፫" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል ::

፪. መቋቋም

፩) ሀዋሳ ዩኒቨርሲቲ (ከዚህ በኋላ "ዩኒቨርሲቲ" እየተባለ የሚጠራ) ራሱን የቻለ የሕግ ሰውነት ያለው የመንግሥት ከፍተኛ ትምህርት ተቋም ሆኖ በዚህ ደንብ እንደገና ተቋቁሟል::

፪) የዩኒቨርሲቲው ተጠሪነት ለትምህርት ሚኒስቴር ይሆናል ::

፫) ዩኒቨርሲቲው በከፍተኛ ትምህርት አዋጅ ቁጥር ፮፻፶/፪ሺ፩ እና በፌዴራል ዩኒቨርሲቲዎች የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፪፻፲ /፪ሺ፫ መሠረት ይተዳደራል ::

ያንዱ ዋጋ
Unit Price 2.30

## COUNCIL OF MINISTERS REGULATION No. 231/2011

## COUNCIL OF MINISTERS REGULATION TO PROVIDE FOR THE RE-ESTABLISHMENT OF THE HAWASSA UNIVERSITY

This Regulation is issued by the Council of Ministers pursuant to Article 5 of the Definition of Powers and Duties of the Executive Organs of the Federal Democratic Republic of Ethiopia Proclamation No. 691/2010 and Article 5(1) of the Higher Education Proclamation No. 650/2009.

1. **Short Title**

This Regulation may be cited as the "Hawassa University Re-establishment Council of Ministers Regulation No. 231/2011."

2. **Establishment**

1) Hawassa University (hereinafter the "University") is hereby re-established as an autonomous higher education public institution having its own legal personality .

2) The University shall be accountable to the Ministry of Education.

3) The University shall be governed by the Higher Education Proclamation No. 650/2009 and the Federal Universities Council of Ministers Regulation No. 231/2011.

ነጋሪት ጋዜጣ ፖ.ሣ.ቁ. ፹ሺ፩
Federal Negarit P.O. Box 80,001

፫. ዋና ግቢ

የዩኒቨርሲቲው ዋናው ግቢ በሀዋሳ ከተማ ሆኖ በሌሎች ቦታዎች የትምህርት ክፍሎች እና የምርምርና የሕብረተሰብ አገልግሎት ማዕከሎችን ሊያቋቁም ይችላል ።

፬. የተሻረ ደንብ

የደቡብ ዩኒቨርሲቲ ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፷፪/፲፱፻፺፪ (በደንብ ቁጥር ፩፻፳፯/፲፱፻፺፱ እንደተሻሻለ) በዚህ ደንብ ተሽሯል ።

፭. ደንቡ የሚጸናበት ጊዜ

ይህ ደንብ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የጸና ይሆናል ።

3. **Main Campus**

The University shall have its main campus at Hawassa and may establish elsewhere other academic units and centers of research and community services.

4. **Repealed Regulation**

The Debub University Establishment Council of Ministers Regulation No. 62/2000 (as amended by Regulation No. 127/2006) is hereby repealed.

5. **Effective Date**

This Regulation shall enter into force on the date of publication in the Federal Negarit Gazeta.

አዲስ አበባ ግንቦት ፲፭ ቀን ፪ሺ፫ ዓ.ም.

መለስ ዜናዊ

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

ጠቅላይ ሚኒስትር

Done at Addis Ababa, this 23rd day of May 2011.

MELES ZENAWI

PRIME MINISTER OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጀት

ሳሙኤል ግርማ
የሕግ አማካሪና ጠበቃ

Samuel Girma
Legal consultant and Attorney

+251911190299